**ምረጫ ቦርድ የትብብር ደብዳቤ ነገ  ከሰዓት በኃላ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፣**

March 11, 2008

ቅንጅት ስሙን ተነጥቆ ሌላ ስም እንዲያወጣ በመገደዱ የቅንጅት አመራር አባላት “አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ’ የሚለውን  ስም ለምርጫ ቦርድ አቅርበዋል። ምርጫ ቦርድ በነገው ለት በ3፡00 PM በአዲስ አበባ ሰዓት የትብብር ደብዳቤ የሰጣል ተብሎ እንደሚጠበቅ የአንድነት ለዲሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ ለሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ዛሬ አስታወቁ።

በተጨማሪም በመጪው ሀሙስ የአንድነት ፓርቲ 50 ለሚሆኑ ግለሰቦች የፊርማ አሰባሰብ ደንብ እና የጠቅላላ ጉባዔ አመራረጥ  መመሪያዎች ስልጠና ከተሰጣቸው በኃላ  ወደ አምስት የተለያዩ የኢትዮጵያ  አቅጣጫዎች እንደሚላኩ አስታውቋል።

የቅንጅት ስም መለወጥ በአገሪቷ የመንግሥትና የግል በተባሉ ጋዜጦች ተቀዳሚ ዜና ሆኖ በመታተሙ ጋዜጦች ህትመታቸውን በጠዋቱ ሸጠው እንደጨረሱ ታውቋል። አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚለው ስም በበርካታ  ኢትዮጵያውያን ተቀባይነት አግኝቷል።